የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፫ ቀን ፪ሺ.፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 31
ADDIS ABABA 21st April, 2022


**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፭፻፱/፪ሺ.፲፬


የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ ደንብ..................... ገጽ ፲፬ሺ.፪፻፩


**Content**

**Regulation No.509/2022**


Definition of Organization, Power and Duties of the Ethiopian Agriculture Authority Regulation ……...............................Page 14201


**ደንብ ቁጥር ፭፻፱/፪ሺ.፲፬**

**የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራትን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፪፻፷፫/፪ሺ.፲፬ አንቀጽ ፵፭ (፪) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ ደንብ ቁጥር ፭፻፱/፪ሺ.፲፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

**Regulation No.509/2022**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DETERMINE THE ORGANIZATION, POWER AND DUTIES OF THE ETHIOPIAN AGRICULTURAL AUTHORITY**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 45 (2) of the Definition of Power and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2021.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as "Definition of Organization, Powers and Duties of the Ethiopian Agriculture Authority Regulation No.509 /2022".

2. **Definition**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 64.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩/ “የምስክር ወረቀት” ማለት ለግብርና ቴክኖሎጂ ወይም ለግብርና ግብዓት ወይም ለግብርና ምርት የብቃት፣ የፍቱንነት፣ የጥራት፣ የደህንነት፣ ፈዋሽነት፣ የጤንነት እና ሌሎች የባለሥልጣኑን መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

1/ “Certificate” means a document issued for verification of compliance with the authority's standards of efficiency, quality, safety, cure, health and other requirements of agricultural technology or agricultural inputs or agricultural production;

፪/ “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት ቁጥጥር በሚያስፈልገው ግብርና ግብዓት ወይም ግብርና ምርት ማምረት ወይም ማዘጋጀት ወይም ግብይት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወይም የግብርና አገልግሎት መስጠት ሥራ ለመሰማራት መስፈርቶች መሟላታቸውን በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ የሚሰጥ ሕጋዊ የምዝገባ ሰነድ ነው፤

2/ “Certificate of Competence” means a legal certificate issued, to those who wish to engage in the production, marketing, import, or export of regulated agricultural inputs or agricultural products or to provide agricultural services, by the Authority upon fulfillment of the requirements;

፫/ “ፈቃድ” ማለት የንግድ ፈቃድን ሳይጨምር ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መሥፈርት ወይም በሥራ ላይ በዋሉ ሕጎች መሠረት በባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር ስር በሚወድቁ እና ፈቃድ ለሚፈልጉ ተግባራት የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

3/ “License” means excluding business licenses; it is a document issued for activities that fall under the Authority’s power and function in accordance with the requirements set by the Authority or any other applicable laws;

፬/ “ምዝገባ” ማለት የግብርና ቴክኖሎጂ፣ የግብርና ግብዓት፣ የግብርና ምርት፣ የግብርና አገልግሎት ወደ ተግባር ከመግባቱ በፊት ተፈላጊ መሥፈርት ማሟላቱን በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ እውቅና የሚሰጥበት ሂደት ነው፤

4/ “Registration” means a process by which agricultural technology, agricultural input, agricultural product and agricultural service are granted recognition being approved by the Authority, fulfilling the necessary requirements, before they can be implemented or utilized;

፭/ “የግብርና ቴክኖሎጂ” ማለት በምርምር የተገኘ በእንስሳት፣ በዕጽዋት እና በግብርና ተፈጥሮ ሃብት መስክ ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ብክነትን ለመቀነስ እንዲሁም ጥራትን እና ጤንነትን ለማሻሻል የሚውል ሆኖ በባለሥልጣኑ ብቁነቱ ተረጋግጦ የተመዘገበ

5/ “Agricultural Technology” is an invention of traditional and scientific research that has been approved and registered by the Authority in the fields of animal, plant and agro-natural resources to increase productivity,

የባህላዊ ወይም ሳይንሳዊ ምርምር ግኝት ነው፤

፮/ "የአዳቃይ መብት ጥበቃ" ማለት የእንስሳት ወይም የዕጽዋት ዝርያ በማፍለቁ ወይም በማበልጸጉ ብቸኛ ባለቤት መሆኑን በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ እንዲጠበቅለት ለሚያመለክት ሰው መሥፈርቶችን ማሟላቱ ተረጋግጦ የሚሰጥ ነው፤

፯/ "የግብርና ግብዓት" ማለት የዕጽዋት ዘር እና የእንስሳት ዘር፣ ፀረ ተባይ፣ ማዳበሪያ፣ መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ፣ የእንስሳት በሽታ ክትባት፣ የእንስሳት ሕክምና መድኃኒቶችና መገልገያ መሳሪያዎች፣ የእንስሳት እርባታ መሣሪያዎች፣ የእንስሳት ምርት እና ውጤቶች ማቀነባበሪያ መሣሪያዎች፣ የእርሻ መገልገያ መሣሪያዎች፣ የሰውነት መከላከያ ትጥቅ፣ መገልገያ መሣሪያዎች፣ የእንስሳት እርድ ቄራዎች ግንባታና መገልገያ መሣሪያዎች፣ የመስኖ መገልገያ መሣሪያዎች፣ ለላቦራቶሪ ምርመራ የሚያስፈልጉ ኬሚካሎች እና ቁሳቁሶች እንዲሁም ባለሥልጣኑ በሕግ ማዕቀፎች የግብርና ግብዓት ብሎ የሚሰይማቸውን ያካትታል፤

፰/ "ፀረ-ተባይ" ማለት፡-

ሀ) የሰውና የእንስሳት በሽታ አስተላላፊዎችን ጨምሮ ማንኛውም ተባይ፤

ለ) በማምረት፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ ወይም በግብይት ሂደት በምግብ፣ በግብርና ምርቶች፣ በእንጨትና የእንጨት ውጤቶች ወይም የእንስሳት መኖ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም የሚያውኩ ተፈላጊ ያልሆኑ የዕጽዋት ወይም የእንስሳት

reduce loss, and improve quality and health;

6/ "Breeder`s Right Protection" means recognition and granting of sole ownership to an applicant conforming that the animal breed or plant variety is generated or developed by the applicant meeting requirements as approved by the Authority;

7/ "Agricultural Inputs" means plant seeds and animal breeds, pesticides, fertilizers, feed and raw materials for feed, veterinary vaccines, veterinary drugs and equipment, animal husbandry equipment, animal production and processing equipment; arm implements, body armor, construction and equipment of abattoirs, irrigation equipment, chemicals and materials needed for laboratory testing, and others that the Authority designates as agricultural inputs within the legal framework;

8/ "Pesticides" means any substances or mixture of substances, or a living organism intended for preventing, destroying or controlling:

a) any pet, including vectors of human or animal diseases;

b) unwanted species of plants or animals causing harm during or otherwise interfering with the production, processing, storage, transport or marketing of food, agricultural commodities, wood and

ዝርያዎችን፣ ወይም

ሐ) በእንስሳት ውጫዊ አካላት የሚከሰቱ ነፍሳትንና ሌሎች ተባዮችን፣

ለመከላከል፣ ለማጥፋት ለመቆጣጠር የሚያገለግል ማናቸውም ንጥረ ነገር ወይም የማናቸውም ንጥረ ነገሮች ድብልቅ ወይም ሕይወት ያለው ነገር ሲሆን፣ የዕጽዋት እድገትን ለመቆጣጠር፣ ቅጠሎችን ለማርገፍ፣ ለማድረቅ ወይም ፍሬዎችን ለማሳሳት ወይም ያለጊዜያቸው እንዳይረግፉ ለመከላከል የሚውሉ ንጥረ ነገሮችን እና ከምርት ስብሰባ በፊትና በኋላ ጥራት እንዳይቀንሱ ለመከላከል የሚያገለግሉትን ንጥረ ነገሮች ያካትታል፤

፱/ "የእንስሳት መድኃኒት" ማለት የእንስሳት በሽታን ለመመርመር፣ ለማከም ወይም ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የውስጥና የውጭ ጥገኞችንና በሽታ አስተላላፊ ተባዮችን ማከሚያ ውህዶችን፣ ባዮሎጂካል ውጤቶችን፣ የሳኒተሪ መገልገያዎችንና የእንስሳት ሕክምና መሣሪያዎችን እንዲሁም ባለሥልጣኑ በሕግ ማቀፎች የእንስሳት መድኃኒት ብሎ የሚሰይማቸውን ያካትታል፤

፲/ "የግብርና ምርት" ማለት በሀገር ውስጥም የተመረተ ሆነ ከውጭ ሀገር የሚቀርብ ያልተዘጋጀ ወይም በከፊል የተዘጋጀ ዕጽዋት፣ የዕጽዋት ውጤቶች፣ መኖ፣ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤትና ተዋጽኦን ወይም የዱር እንስሳት ምርትና ተረፈ ምርት፣ ደንና የደን ውጤቶች፣ ዓሣ፣ማርና የማር ውጤቶችን ወይም ባለሥልጣኑ በሕግ ማዕቀፎች የግብርና ምርት ብሎ የሚሰይማቸውን ያካትታል፤

wood products or animal feed stuffs; or

c) insects or other pests on bodies of animals;

and includes substances intended for use as a plant growth regulator, defoliant, desiccant, or agent for thinning fruit or preventing the premature fall of fruit, and substances applied to crops either before or after harvest to protect the commodity from deterioration during storage and transport;

9/ "Veterinary Drug" means any substance or mixture of substance used to diagnose, treatment, or prevention of animal disease and includes products used to treat internal and external parasites and diseases transmitting vectors, biological products, sanitary items, and veterinary equipment, as well as others that the Authority designates as veterinary drugs within the legal framework;

10/ "Agricultural Product" means locally produced or imported unprocessed or semi-processed plant, plant product, feed, animal, animal product and by-products or wildlife products, forest and forest products, fish, honey and honey product or others that the Authority designates as agricultural product based on legal framework;

፲፩/ "ያልተዘጋጀ የግብርና ምርት" ማለት እንደ ተመረተ ጥሬ ሆኖ የተቆራረጠ፣ የተከፋፈለ፣ የተቀነጣጠበ፣ የቀዘቀዘ፣ በንጥረ ነገር ያልበለጸገ፣ ያልደረቀ፣ ጨው ያልገባበት እና በሌሎች ተፈጥሮአዊ ይዘቱን በማይለውጡ ተመሳሳይ ሂደቶች አልፎ የታሸገም ሆነ ያልታሸገ የግብርና ምርት ያካተተ ነው፤

፲፪/ "በከፊል የተዘጋጀ የግብርና ምርት" ማለት የተበጠረ፣ የተፈተገ፣ የተከፋፈለ፣ የተላጠ፣ የተፈለፈለ፣ በንጥረ ነገር ያልበለጸገ፣ ያልደረቀ፣ ጨው ያልገባበት እና በሌሎች ተፈጥሮአዊ ይዘቱን በማይለውጡ ተማሳሳይ ሂደቶች አልፎ የታሸገም ሆነ ያልታሸገ የግብርና ምርት ያካተተ ነው፤

፲፫/ "የግብርና አገልግሎት" ማለት የብቃት ማረጋገጫ ወይም ፈቃድ እና ቁጥጥር በሚፈልጉ የግብርና ምርምር፣ የግብርና ኤክስቴሽን-ማማከር አገልግሎት፣ የመካናይዜሽን አገልግሎት፣ የመካናይዜሽን ጥገና ወይም በባለሥልጣኑ አገልግሎቶች ተብለው በሕግ የሚወሰኑ ናቸው፤

፲፬/ "የግብርና ሬጉላቶሪ አገልግሎት መስጫ ማዕከል" ማለት የግብርና ቴክኖሎጂ ልየታ፣ ብቃትና ፍቱንነት ፍተሻ ጣቢያ፤ ላቦራቶሪ፣ ግብርና መካናይዜሽን ሙከራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል፣ የመግቢያና መውጪያ ፍተሻ ኬላ፣ ቄራ፣ ድህረ-መግባት ኳራንቲን ጣቢያ፣ ኳራንቲን ጣቢያ፣ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት እንዲሁም ሌሎች የሬጉላቶሪ ሥራ የሚሰራበት ነው፤

11/ "Unprocessed agricultural product" is defined as agricultural products being produced in raw form or subsequently sliced, pulverized, chilled, unaffected, undried, untreated by additive, salt and otherwise sealed or unsealed by other similar processes;

12/ "Semi-processed agricultural product" is defined as agricultural products being produced in raw form or subsequently refined, peeled, unaffected, undried, untreated by additive, salt and otherwise sealed or unsealed by other similar processes;

13/ "Agricultural Service" means services provided by an Agricultural Research, Agricultural Extension-Advisory service, Mechanization services and Mechanization Maintenance or any other service designated as agricultural services by the Authority that requires license or certificate and monitorig;

14/ "Agricultural Regulatory Service Provision Center" means an agricultural technology characterization, competency & efficacy testing center, laboratory, agricultural mechanization testing and certification center, entrance and exit checkpoint, abattoirs, post-entry quarantine station, quarantine station, branch offices and other areas where regulatory service is provided;

፲፭/ “ኢንስፔክተር” ማለት የግብርና ቴክኖሎጂን፣ የግብርና ግብዓትን፣ የግብርና ምርትንና የግብርና አገልግሎት ውጤታማነትን፣ ፍቱንነትን፣ ጥራትን፣ ደህንነትንና ጤንነትን አስመልክቶ በወጡ መስፈርቶች እና የሕግ ማዕቀፎች መሠረት የሬጉላቶሪ ተግባር እንዲያከናውን የሚመደብ ባለሙያ ነው፤

፲፮/ “ሬጉላቶሪ” ማለት የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብርና ግብዓት፣ ግብርና ምርትና ግብርና አገልግሎት ሊኖረው የሚገባውን ብቃት፣ ፍቱንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራት፣ ደህንነት ወይም ጤንነት በተደራጀ መረጃ፣ የባለሙያ ግምገማ፣ በመስክ ምልከታ ወይንም ሙከራ ወይም በላቦራቶሪ ምርመራ በተቀመጠ መስፈርት ወይም የግብርና ደረጃ መሰረት የሚረጋገጥበት፣ የሚመዘገብበት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ነው፤

፲፯/ “ኳራንቲን” ማለት የዕጽዋት እና የዕጽዋት ውጤቶች፣ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች እና ተዋጽኦ እንዲሁም ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶችን ለክትትልና ምርምር፣ ለተጨማሪ ኢንስፔክሽን ወይም ለማከም ኦፊሴላዊ በሆነ መንገድ ለተወሰነ ጊዜ ማግለል ማለት ነው፤

፲፰/ “የግብርና ስታንዳርድ” ማለት ቁጥጥር በሚደረግባቸው የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብርና ግብዓት፣ ግብርና ምርትና ግብርና አገልግሎት የሚፈለገን ዝቅተኛ የብቃት፣ ፍቱንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራት፣ ደህንነትና ጤንነት ደረጃን ወይም መስፈርትን ለመለካት የተዘጋጀ ሰነድ ነው፤

15/ “Inspector” is a professional who is assigned to conduct regulatory activities according to pre-set requirements and laws that state about performance, efficacy, quality, safety and health of agricultural technology, agricultural input, agricultural products and agricultural services;

16/ “Regulatory” is a system of approval, registration and control based on organized information, expert evaluation, field observation or laboratory testing to ensure whether an agricultural technology, agricultural input, agricultural product and agricultural service has the expected performance, efficacy, quality, safety or health as compared to pre-set requirements and agricultural standards;

17/ “Quarantine” means an official confinement of plants, plant products, animals and animal products and other controlled materials for monitoring, research, further inspection or treatment for a specified length of time;

18/ “Agricultural Standard” is a document prepared to measure the minimum efficiency, performance, efficacy, quality, safety and health requirements for regulated agricultural technology, agricultural inputs, agricultural product and services;

፲፱/ "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ነው፤

፳/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፳፩/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፳፪/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፫/ በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፫. ዓላማ

በግብርና ዘርፉ የተጠናከረ ሬጉላቶሪ ሥርዓት በመዘርጋት እና በመተግበር በዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ በሰው፣ በእንስሳት እና በዕጽዋት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ላይ ጎጂ ተጽዕኖ እንዲቀንስ ወይም እንዲወገድ ማስቻል፡፡

፬. ዋና መስሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤቱ አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወይም የግብርና ሬጉላቶሪ ማዕከላት ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባራት

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በግብርና አገልግሎት ላይ እንዲሁም በግብርና ግብዓት እና ምርት ማምረትና ግብይት፣ የሙያ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መስፈርት ያዘጋጃል፣ በመስፈርቱም መሠረት

19/ "Authority" means the Ethiopian Agriculture Authority;

20/ "Ministry or Minister" means the Ministry of Agriculture or its Minister, respectively;

21/ "Region" means any state referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and including the Addis Ababa City Administration and Dire Dawa Administrations;

22/ "Person" means any natural person or legal entity;

23/ The provisions expressed in masculine in this Regulation include the feminine gender.

3. Objective

Establish and implement a strong regulatory system in the agricultural sector to improve international and national competitiveness, minimize or eliminate harmful impact on human, animal and plant health and environment.

4. Head Office

The Authority shall have its Head office in Addis Ababa and may have branch offices and Regulatory centers elsewhere, as may be necessary.

5. Powers and Duties of the Authority

The Authority shall have the following power and duties:

1/ Prepares professional licensing and certificate of competence requirements for agricultural services, agricultural input, product and marketing; issue;

ፈቃድ ይሰጣል፤ እንደአስፈላጊነቱ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

፪/ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ ማምረትና ንግድ ተቋማት ውስጥ ለሚሰማሩ ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ እንደአስፈላጊነቱ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

፫/ የግብርና ግብዓት ወይም ምርት ከውጭ ሀገር ለሚያስገቡ ወይም ለውጭ ሀገር ገበያ ለሚያቀርቡ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ይመዘግባል፤ እንደአስፈላጊነቱ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

፬/ በሀገር ውስጥ ከአንድ ክልል በላይ ለሚደረግ የግብርና ግብዓት እና የግብርና ምርትን ማምረት፣ የግብይት ተግባር ሲኖር የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፣ ይመዘግባል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

፭/ ከውጭ የሚገባና በሀገር ውስጥ የሚበለጽግ የግብርና ቴክኖሎጂ ብቃትን ይፈትሻል፣ ይመዘግባል፣ በአመልካች ሲጠየቅም መርምሮ የአዳቃዮች ባለቤትነት መብት ጥበቃ ይሰጣል፤ ያስተዳድራል፤

፮/ የግብርና ግብዓትን እና የግብርና ምርትን ፍቱንነት፣ ጥራት፣ ውጤታማነት፣ ደህንነት በመሥፈርቶችና በግብርና ደረጃዎች መሠረት በመገምገም የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ጥቅም ላይ እንዲውል ክትትል ያደርጋል፤ እንደአስፈላጊነቱ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤

፯/ የእንስሳት እና የዕጽዋት ግብዓት ምርት ማምረቻ፣ ማዘጋጃ፣ ማቀነባበሪያ፣ ማከማቻ፣ ጅምላ መሸጫ ቦታዎችን በመስፈርት እና በወጡ የግብርና ስታንዳርዶች መሠረት የብቃት

renew, suspend or revoke license as may be necessary;

2/ Issues, as may be necessary, renews, suspends and cancels licenses to professionals engaged in veterinary drug and feed production and trade;

3/ Provides and registers certificate of competence to importers or exporters of agricultural inputs or agricultural products, as may be necessary, renews, suspends and cancels such certificates;

4/ Issues and registers competence of certificate for activities run related to agricultural input, agricultural production, and marketing activities in more than one region within the country; renews, suspends and cancels the certificate;

5/ Tests the performance of imported and locally developed agricultural technology and registers such; grants and administers breeder's right upon request by an applicant and conducting the necessary examination;

6/ Issues quality certificate for agricultural inputs and agricultural products after evaluating for performance, efficacy, efficiency, quality or safety according to requirements and agricultural standards and suspends or revoke the certificate as may be necessary;

7/ Issues certificate of competency to livestock and plant products production, processing plant, storage, wholesale areas in accordance with requirements

ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡ እንደአስፈላጊነቱ ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤

፰/ በሥራ ላይ ያሉትንና ከግብርና ግብዓት እና ምርት ጥራት፣ ፍቱንነት፣ ደህንነትና ጤንነት ጋር ተያያዥ የሆኑ የግብርና ስታንዳርዶችን ተግባራዊ ያደርጋል፤ እንደአስፈላጊነቱም ያሻሽላል፡ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበርም አዳዲስ ያወጣል፤

፱/ የግብርና አገልግሎት አሰጣጥን እንዲሁም የግብርና ግብዓትና ምርት አመራረትና ግብይት የሀገሪቱንና እንደአስፈላጊነቱም የዓለም አቀፍ የጥራት፣ የኳራንቲን ደህንነትን ስታዳርዶች አሟልተው እየተከናወኑ መሆኑን በመስክና በላቦራቶሪ ምርመራ ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ እንደአስፈላጊነቱም በሌላ አካል እንዲረጋገጥ ያደርጋል እንዲሁም ተቀባይነት ያለው የዕጽዋት ወይም የእንስሳት ጤና ሰርተፊኬት ይሰጣል፤

፲/ በውጭ ሀገር ተመርተው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡና ቁጥጥር የሚደረግበት የግብርና ግብዓትና ምርት በተመለከተ በወጡ የሕግ ማዕቀፎች ጥራት፣ ጤንነት እና ደህንነት መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ ቅድመ-የማስገቢያ ፈቃድ እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ የመልቀቂያም ፈቃድ ይሰጣል፤ መስፈርቱን ካላሟላ ያግዳል፡ ወይም እንዲታከም ወይም እርምት እንዲደረግበት ወይም አስፈላጊ ከሆነም እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት ሀገር እንዲመለስ ያደርጋል፤

፲፩/ በሀገር ውስጥ ተመርተው ለውጭ ሀገር ገቢያ የሚቀርቡ የግብርና ግብዓቶችና ምርቶች የዓለም አቀፍ ወይም የተቀባይ ሀገር የጥራት፣ ጤንነትና ደህንነት ስታንዳርድ ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ዓለም አቀፍ የዕጽዋት ወይም የእንስሳት ጤና

agricultural standards; renews, suspends and revoke as may be necessary;

8/ Implements existing Agricultural standards related to agricultural inputs and agricultural products quality, efficacy, safety and health; amends as needed; and issues new standards in collaboration with Ethiopian Standard Institute;

9/ Ensures agricultural service provision, agricultural input production and agriculture production and marketing are implemented according to national or international quality health, food safety standards through field inspection and laboratory testing or through third party service providers; as necessary and issues a valid plant or animal health certificate;

10/ Ensures that imported and regulated agricultural inputs and products meet the legal requirements of quality, health and safety; issue pre import permit and import release permit and export permit; If it does not meet the requirement, suspends, or orders treatment or corrective measure or, if necessary, dispose off or return to the country of origin;

11/ Issues, renews, suspends or revokes, as may be necessary, an international health certificate to agricultural inputs and products, produced locally and destined for export, approving that they

ሠርተፍኬት ይሰጣል፣ ይመዘግባል፤ እንደአስፈላጊነቱ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

፲፪/ በባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ባገኘ ሰው በሀገር ውስጥ ተመርቶ ወይም ተዘጋጅቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀርብ የግብርና ግብዓትና ምርት ባለሥልጣኑ ከሚመለከተው ተቋም ጋር በሚያወጣው የጥራትና ጤንነትና ደህንነት ስታንዳርድ መሠረት ምርመራ በማካሄድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይመዘግባል፣ እንደአስፈላጊነቱ ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤

፲፫/ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ የሬጉላቶሪ እና የኳራንቲን ቁጥጥር መርሆዎች እና ስምምነቶች እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

፲፬/ ለግብርና ዓብዓት ምርትና አገልግሎት የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ እንደአስፈላጊነቱም መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ያደርጋል፣ የመረጃን ትክክለኛነትና አግባብነት ያረጋግጣል፣ አሻሚ ወይም ትክክለኛ ያልሆኑ መረጃዎች እንዳይሰራጩ ያደርጋል፤

፲፭/ የባለሥልጣኑ ግብርና ሬጉላቶሪ አገልግሎቶች እንዲቋቋሙ፣አቅማቸው እንዲገነባና እንደ አስፈላጊነቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፲፮/ የግብርና ግብዓት ወይም ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝር ተግባራዊ ያደርጋል፤ በየዓይነታቸው ይመድባል፤ መዘርዝሮችንም በየጊዜው ይከልሳል፤ አዳዲሶችንም ያዘጋጃል፤

፲፯/ የዕፅዋት ኳራንቲን ተባይና በሽታ እንዲሁም ድንበር ተሻጋሪ የእንስሳት በሽታ ቅኝት፣ አሰሳ እና የስጋት ትንተና ያካሂዳል፤ የአሠራር መመሪያ ያዘጋጃል፤ ሥርዓት ይዘረጋል፤

fulfill international or importing country`s standards for quality, safety and health;

12/ Agricultural inputs and products produced locally by a person holding certificate of competence, are certified in accordance with the quality and health standards set by the authority and relevant body by conducting inspection, testing and registers, certifies, renew, suspend and revoke the certificate as may be necessary;

13/ Cause to implement international, continental and regional regulatory and quarantine principles and agreements.

14/ Serves as a data center for agricultural inputs, products and services, makes information accessible to users as necessary, verifies the accuracy and relevance of information, and prevents the dissemination of ambiguous or inaccurate information;

15/ Establishes and capacitates the Authority's agricultural regulatory services, and endeavor to gain international recognition or accreditation as may be necessary;

16/ Implement the list of agricultural inputs and additives; categorize each of them, based on their type, regularly review lists, and prepares new ones;

17/ Conducts plant quarantine pests and diseases surveillance, as well as trans boundary animal disease surveys, carries out risk analyses; and sets up a system and prepare a Directive;

፲፰/ የዕፅዋትና እንስሳት ኳራንቲን ግልጋሎት የሚሰጥ የቅድመ እና ድህረ መግባት ኳራንቲን እና የዘር-ድህረ ጥራት ቁጥጥር ጣቢያዎች ያቋቁማል፤ ያደራጃል፤

፲፱/ የዕፅዋትና እንስሳት ተባይና የበሽታ ስርጭት ጥናት በማድረግ ሀገራዊ የኳራንታይን ተባይና በሽታ መዘርዝር ያዘጋጃል፤

፳/ የዕፅዋት እና የእንስሳት ግብዓቶች ከተመዘገቡ በኋላ በክምችት በማጓጓዝ፣ በስርጭት፣ በግብይት፣ በአጠቃቀም እና በአወጋገድ ወቅት አግባብነት ባለው የሕግ ማዕቀፍ መሠረት ይቆጣጠራል፤

፳፩/ እንስሳትን እና የእንስሳት ውጤት፣ የእንስሳት ተዋጽኦ እና መኖ እንዲሁም ዕጽዋት እና የዕጽዋት ምርት ከሬጉላቶሪ አኳያ ይለያል፤ ይመዘግባል፤ እንደአስፈላጊነቱ የኋላ ታሪክ ያጠናል፤ ይከታተላል፤

፳፪/ ባለሥልጣኑ በዓለምአቀፍ ደረጃ እና በሌሎች ሀገሮች ተቀባይነት ያላቸውን የጋራ ስምምነቶች፣ ደረጃዎችንና የሬጉላቶሪ ዘዴዎች እንደ አስፈላጊነቱ ተቀብሎ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፤ ለአተገባበራቸውም በሕግ መሠረት ይፈራረማል፤

፳፫/ በዚህ ደንብ ቁጥጥር የሚደረግበት የግብርና ግብዓት ወይም ምርት ይህንን ደንብ ወይም በሌሎች ሕጎች መሠረት ሊሟሉ የሚገባቸውን ሳያሟላ ሲቀር እንደአግባቡ ምርቱን ወይም ግብዓቱን ሊይዝ፣ እንዲወገድ ሊያደርግ፣ ከገበያ እንዲሰበሰብ ሊያዝ፣ በሕግ አግባብ ሊወርስ ይችላል፤

፳፬/ በባለሥልጣኑ እውቅና ተመዝግቦ ገበያ ውስጥ እንዲገባ የተደረገ ግብርና ግብዓትና ምርት በሚመለከት ይከታተላል፣ ናሙና ይወስዳል፣ ይመረምራል፤አሉታዊ ውጤት ሲከሰት አግባብ

18/ Establishes and organizes pre and post entry Plant and Animal quarantine posts and plant seed post control stations;

19/ Prepares national quarantine pest and disease list by studying plant and animal pests and diseases prevalence;

20/ Regulates plant and animal inputs after registration during storage, transportation, distribution, marketing, use and disposal in accordance with appropriate legal framework;

21/ Identifies, registers and monitors animals, animal products, animal bi-products, feed, plants and plant products from regulatory perspective; studies and monitors their traceability as may be necessary;

22/ The Authority may adopt and implement internationally and other country`s recognized agreements, standards and regulatory mechanisms as necessary; signs an agreement in accordance with the law;

23/ Agricultural inputs or products regulated by this Regulation may be seized, disposed off, recollect from market, or confiscate by law if they do not comply with the requirements of this Regulation or any other laws;

24/ Monitors, draws sample from agricultural input and product registered by the Authority that enters into market; and conducts tests and

ካለው የክልል ባለሥልጣን ጋር በመተባበር እርምጃ ይወስዳል፤

፳፭/ የግብርና ግብዓትና ምርት የሬጉላቶሪ መስፈርት ባለማሟላቱ ምክንያት በአካባቢ፣ በሰው፣ እንስሳት እና በዕጽዋት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያደረሰ እንደሆነ ጥናት ያደርጋል፣ ውጤቱን መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ አግባብ ካለው የክልል ባለሥልጣን ጋር በመተባበር እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፳፮/ የእንስሳት መድኃኒት ወይም ክትባት፣ ጸረ ተባይ እና ማዳበሪያ ላይ የሚካሄዱ የመስክ ሙከራ ጥያቄዎችን እየመረመረ ይፈቅዳል፣ ሙከራው በመልካም የእንስሳት ህክምና እና ግብርና ሥርዓት መሠረት መካሄዱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ገንቢ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ አስፈላጊ ሲሆን ሙከራው እንዲታገድ ወይም እንዲቆም ትዕዛዝ ይሰጣል፤

፳፯/ የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበትን፣ ምንጩ ያልታወቀን፣ ከባዕድ ነገር ጋር የተቀላቀለ ወይም መስፈርትን የማያሟላ የግብርና ግብዓት እና ምርት ይወርሳል፤ መወገድ ያለበትን ግብዓት ወይም ምርት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲወገድ ያደርጋል፤ በአግባቡ መወገዱንም ይቆጣጠራል፤

፳፰/ ሕይወት ያለው ደቂቀ ዘ-አካላት ወይም እንስሳት ወይም ዕጽዋት ከውጭ ሀገር ሲገባ መርምሮ የመግቢያ ፈቃድ ይሰጣል፤ የሀገር ውስጥ ብዝሀ ሕይወት ከውጭ በሚገቡ ባዕድ ወራሪ ዝርያዎች ጥፋት እንዳይደርስበት ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፤ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለሀገር ውስጥ ብዝሃ ሕይወት የአርክቦት ፈቃድ ይሰጣል፤

takes action in collaboration with regions on negatively ending results;

25/ Assess adverse effects of agricultural inputs and products on the environment, human beings, animals and plants due to non-compliance with the regulatory requirements, and based on the results, take the necessary legal action in collaboration with the appropriate regional authority;

26/ Assesses and gives permit to field trial requests on veterinary drugs or vaccine, pesticides or fertilizer; monitors and regulates that the trials are carried out according to good animal and agricultural practices; forwards constructive recommendations orders trial suspension or termination as may be necessary;

27/ Confiscate agricultural inputs and products that are counterfeit, out of date, of unknown origin, adulterated with foreign matter or that do not meet requirements; it shall remove non-conforming input or product along with an appropriate bodies and monitors proper disposal;

28/ Issues import permit to a sample of any micro-organism or animal or plant life forms when imported from foreign countries; regulates and monitors domestic biodiversity to prevent from any adverse effect by invasive alien spices; authorize access to genetic resources based on available laws;

፳፱/ ሥልጣንና ተግባሩን ለማስፈጸም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ኢንስፔክተሮችን ይመድባል፤

፴/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ይሰበስባል፤

፴፩/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፡፡

## ፮. <u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ፡-

፩/ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

፪/ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች፣ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል፡፡

## ፯. <u>የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባራት</u>

፩/ ዋና ሥራ አስፈጻሚው የባለሥልጣኑን ሥራዎች ያቅዳል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የባለሥልጣኑን ዓመታዊ እቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና እቅድ መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

29/ Assigns the necessary inspectors to carry out its power and duties;

30/ Collects service fees in accordance with the rate determined by Council of Ministers;

31/ Owns property, enter into contracts, sue and be sued in its own name.

## 6. <u>Organizational structure of the Authority</u>

The Authority shall have:-

1/ A Chief Executive Officer

2/ Deputy Chief Executive Officers as required; and

3/ The necessary staffs.

## 7. <u>Power and Duties of the Chief Executive Officer</u>

1/ The Chief Executive Officer shall plan, direct and manage the activities of the Authority:

2/ Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Chief Executive Officer shall;

a) exercise the power and duties of the Authority stated under Article 5 of this Regulation;

b) employ and administer employees of the Authority in accordance with the Federal Civil Service laws;

c) prepare the work program and budget of the Authority, and implement the same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Authority;

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ) የባለሥልጣኑን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል::

፫/ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል::

፰. <u>የምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባራት</u>

ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡-

፩/ የሚመራውን ዘርፍ ተግባራት ያቅዳል፣ ይመራል፤ ያስተባብራል፤

፪/ በዋና ሥራ አስፈጻሚው ሲወከል ዋና ሥራ አስፈጻሚውን ተክቶ ይሰራል፤ ካልወከለ ቅድሚያ አገልግሎት ያለው ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ተክቶ ይሰራል፤

፫/ በዋና ሥራ አስፈጻሚው ተለይቶ የሚሰጠውን ተጨማሪ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

፱. <u>በጀት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል::

፲. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

፩/ ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

e) represent the Authority in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Authority.

3/ The Chief Executive Officer may delegate part of his power and duties to the officials and employees of the Authority to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Authority.

8. <u>Power and Duties of Deputy Chief Executive Officers</u>

The Deputy Chief Executive Officer shall have the following power and duties:

1/ Plans, directs and coordinates the activities of the sub-sector it leads;

2/ In the absence of the Chief Executive Officer and upon delegation shall act in place of the Chief Executive Officer; failing such delegation a Deputy Chief Executive Officer with the longest tenure shall be designated.

3/ Perform any other duties assigned by the Chief Executive Officer.

9. <u>Budget</u>

The budget of the Authority shall be allocated by the Government;

10. <u>Book of Accounts</u>

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts;

፪/ የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

**፲፩. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

2/ The book of accounts of the Authority shall be audited annually by the Federal Auditor General or by an Auditors assigned by the Auditor General.

**11. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 21st Day of April, 2022.**

**ABIY AHMED (DR.)**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**